በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የአደጋ ስጋት ስራ አመራር ኮሚሽን
THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA
DISASTER RISK MANAGEMENTE COMMISSION

ቀን ሐምሌ 09 2018
Date
ቁጥር ሃ11-ዐሁዐ-52/656
Ref No

የኢንዱስትሪ ሚኒስቴር ሚኒስትር

አዲስ አበባ

በአገራችን የተፈጥሮና የሰው-ሰራሽ አደጋ ሲከሰት አስፈላጊ የሆነውን ሰብዓዊ ድጋፍ በራስ አቅም ምላሽ ለመስጠት የሚያስችል የኢትዮጵያ አደጋ ስጋት ምላሽ ፈንድ በአዋጅ ቁጥር 1386/2017 እና በሚንስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 576/2018 መቋቋሙ ይታወሳል።
ከነዚህ የገቢ ምንጮች ውስጥ የትምባሆ፣ አልኮል አምራቾችና አስመጭዎች የሽያጫቸውን 5 በመቶ፤ ኬሚካል አምራችና አስመጭዎች ደግሞ የሽያጫቸውን 1 በመቶ ለፈንዱ እንዲሁም የአክሲዮን ድርጅቶች ለአባሎቻቸው ከሚያከፋፍሉት የዲቪደንድ ገቢ 1 በመቶ አስተዋጽኦ እንዲያደርጉ ተደንግጓል።

መ/ቤታችን በአዋጁና ደንቡ በተሰጠው ሥልጣን መሰረት ከየካቲት 1/2018 ጀምሮ የፈንዱን ገቢ በመሰብሰብ ላይ ይገኛል። በዚህ መሰረት የትምባሆ፣ አልኮልና ኬሚካል አምራቾችና አስመጭዎች እንዲሁም የአክሲዮን ድርጅቶች የሚጠበቅባቸውን የፈንዱን ገቢ እንዲከፍሉ ለማድረግ የሚያስችሉ ስርዓቶችን በመዘርጋት ላይ እንገኛለን።

በዚህ ረገድ አምራቾችና ከላይ የተገለጹት አስመጭዎች የሚጠበቅባቸውን እንዲከፍሉ ለማስቻል በየዓመቱ የንግድ ፈቃዳቸውን ሲያድሱ በአለፈው ዓመት ውስጥ ለአደጋ ስጋት ፈንድ መሰብሰብ ያለባቸውን ገቢ ሰብስበው ለፈንዱ አካውንት ገቢ ማድረጋቸውን የሚገልጽ ማስረጃ ንግድ ፈቃዳቸውን ለሚያድሰው የመንግሥት አካል እንዲያቀርቡ እንደ ቅድመ-ሁኔታ መጠየቅ የፈንዱን ገቢ አሰባሰብ የሚያሳልጥ ይሆናል።

ይህ አሰራርም የትምባሆ፣ አልኮልና ኬሚካል አምራቾችና አስመጪ ድርጅቶችና ግለሰቦች እንዲሁም የአክሲዮን ድርጅቶች የ2020 ዓመታዊ የንግድ ፈቃዳቸውን ሲያድሱ ተግባራዊ ይሆናል። ይህ ደግሞ ድርጅቶቹ ከሀምሌ 2018 ጀምሮ የሚሰበስቡትን ገቢ ታሳቢ የሚያደርግ በመሆኑ አሰራሩን ከወዲሁ ተገንዝበው የተጣለባቸውን ኃላፊነት እንዲወጡ ከወዲሁ ማስገንዘብ ጠቃሚ ይሆናል።

ፋክስ ቁጥር 011-5514788
Fax No. 011-4424974
P.O.BOX 5656
Addis Ababa- Ethiopia
ስልክ ቁጥር
Tel.No 0115-516407
0115524272
Website https://www.edrmc.gov.et

እባክዎን መልስ ሲሰጡ የደብዳቤያችንን ቁጥር ይጥቀሱ
Please quote our Ref.No when replying

## በኢትዮጵያ አደጋ ስጋት ምላሽ ፈንድ ገቢ አሰባሰብን አስመልክቶ የተሰጠ ማሳሰቢያ

በኢትዮጵያ አደጋ ስጋት ምላሽ ፈንድ ማቋቋሚያ አዋጅ ቁጥር 1386/2017 እና በሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 576/2018፣

1. የትምባሆና አልኮል አምራቾችና አስመጭዎች ከሚያከናውኑት ሽያጭ 5 በመቶ፤
2. የኬሚካል አምራቾችና አስመጭዎች ከሽያጫቸው 1 በመቶ፣
3. የአክሲዮን ድርጅቶች ከአባሎቻቸው ዓመታዊ የዲቪደንድ ድርሻ 1 በመቶ ለፈንዱ አስተዋጽኦ እንዲያደርጉ መደንገጉ ይታወቃል፡፡

በዚህ መሰረት የተጠቀሱት አምራቾችና አስመጪዎች እንዲሁም የአክሲዮን ድርጅቶች የፈንዱን ገቢ ከደንበኞቻቸው ሰብስበው በተቀመጠው የጊዜ ሰሌዳ በብሄራዊ ባንክ በተከፈተ የፈንዱ አካውንት ቀጥር 0101961040008 ወይም በንግድ ባንክ አካውንት ቁጥር 1000760129708 ለፈንዱ ገቢ ማድረግ ይጠበቅባቸዋል፡፡

በዚህ መሰረት የትምባሆ፣ አልኮልና ኬሚካል አምራቾችና አስመጪ ድርጅቶችና ግለሰቦች የ2020 በጀት ዓመትን የንግድ ፈቃድ ለማደስ ለአደጋ ስጋት ምላሽ ፈንድ ገቢን ከሀምሌ 2018 እስከ ሰኔ 2019 ዓ.ም. ከሽያጫቸው እንዲሁም የአክሲዮን ድርጅቶች ደግሞ ከዓመታዊ ዲቪደንድ ድርሻ ሰብስበው ለፈንዱ ገቢ ያደረጉበትን ማስረጃ ማቅረብ ለሚቀጥለው ዓመት የፈቃድ ዕድሳት እንደ ቅድመ-ሁኔታ የሚጠየቅ መሆኑን በማወቅ ከወዲሁ ግዴታችሁን እንድትወጡና ማስረጃዎችን እንድትይዙ እናሳስባለን፡፡

በመሆኑም የትምባሆ፣ አልኮልና ኬሚካል አምራቾችና አስመጪ ድርጅቶችና ግለሰቦች እንዲሁም የአክሲዮን ድርጅቶች የ2020 በጀት ዓመትን የንግድ ፈቃድ ለማደስ የታክስ ግዴታቸውን ከመውጣታቸው በተጨማሪ ለአደጋ ስጋት ምላሽ ፈንድ ገቢን ከሀምሌ 2018 እስከ ሰኔ 2019 ከሽያጫቸው ሰብስበው ለፈንዱ ገቢ ያደረጉበትን ማስረጃ እንዲያቀርቡ የሚጠየቁ መሆኑን ከወዲሁ እንዲገለጽላቸው ትብብራችሁን እየጠየቅን የማሳሰቢያውን መነሻ አባሪ የላክን መሆኑን እናሳውቃለን።

ከሠላምታ ጋር

አምባሳደር ዶ/ር ሽፈራው ተ/ማርያም
ኮሚሽነር

<u>ግልባጭ</u>

- ለጠቅላይ ሚኒስትር ጽ/ቤት
- ለኢትዮጵያ አደጋ ስጋት ስራ አመራር ኮሚሽን
- ለአደጋ ስጋት ምላሽ ፈንድ ቦርድ ጽ/ቤት

  <u>አዲስ አበባ</u>